# LATENT TB INFECTION (LTBI) (ድብቅ የ ቲቢ በሽታ)

# ለአደጋ ተጋላጭ ኖት?

## 1. ይገምግሙ

ከሚከተሉት ውስጥ እርሶን የሚመለከት ካለ የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ምርመራ ማድረግ አለብዎ።

እርሶ፤

- ቲቢ በሰፋት የሚገኝባቸው አከባቢዎች ላይ- አፍሪካን፣ ኤሽያን፣ ሜክሲኮን፣ ማዕከላዊ ወይም ደቡብ አሜሪካን፣ ካሪቢያንን እና ምስራቃዊ አውሮፓን ጨምሮ ተወልደው፣ ኖረው(ለ አንደ ወር እና ከዛ በላይ) ወይም ወደ ነዚህ አከባቢዎች በተደጋጋሚ ተጉዘው ከሆነ።
- ከአንድ የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ካለበት ሰው ጋር ጊዜ አሳልፈው ከሆነ
- ለሶስት ሳምንታት ወይም ከዛ በላይ የቆየ ሳል፣ ትኩሳት፣ የ ደረት ህመም፣ የ ክብደት መቀነስ፣ ሌሊት ላይ ማላብ፣ ድካም ወይም የምግብ ፍላጎት መቀነስን ጨምሮ የቲቢ በሽታ ምልክቶች ካለብዎት፤
- ኤች ኣይ ቪ ህመም ካለብዎ፣የ ሰውነት አካል ንቅለ ተከላ ያደረጉ ከሆነ፣ ወይም የሰውነትዎ በሽታ የመከላከል አቅም የሚቀንስ መድሃኒት እየወሰዱ ከሆነ፤
- በመርፌ የሚሰጡ መድሃኒቶች የሚወሰዱ ከሆነ፤
- ብዙ የሰው ሰብሰብ ባለባቸው ቦታዎች ላይ፣ ለምሳሌ እንደ የ ቤት አልባ ሰዎች መጠለያዎች፣ የማረሚያ ቦታዎች፣ እና የነርሲንግ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ወይም የሚኖሩ ከሆነ።



## 2.ምርመራ

የህመም ስሜት ባይሰማዎትም እንኳን፣ በሰውነትዎ ውስጥ የቲቢ ጀርሞች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም ማለት **LTBI** (ድብቅ የቲቢ በሽታ) ሊኖርብዎ ይችላል፣ ከዚህም በተጨማሪ በሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ የመያዝ አደጋ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ።

የቲቢ ጀርሞች ሰውነት ውስጥ መኖር አለመኖር ለመለየት የሚያገለግሉ ሁለት ዓይነት ምርመራዎች አሉ:- የቲቢ የደም ምርመራ እና የቲቢ የቆዳ ምርመራ።

## 3.ህክምና

የምርመራ ውጤትዎ አወንታዊ (ፖዘቲቭ) ከሆነ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ የደረት ራጅ እንዲነሱ ያዞታል።

**Latent TB**(ድብቅ ቲቢ) ካለብዎ፣ ቤተሰብዎ፣ ጓደኞችዎ እና ማሕበረሰብዎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር በሚችል የሚታይ ወይም ንቁ የቲቢ በሽታ ከመታመምዎ በፊት ራሰዎን ለመከላከል የታዘዘልዎትን መድሃኒት መውሰድ አለብዎ።



**Latent TB. Active Concern.**
**Tuberculosis Program**

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ

ድህረ ገጽ፤ www.vdh.virginia.gov/tuberculosis/

ወይም በ 804-864-7906 ወይም tuberculosis@vdh.virginia.gov ተጠቅመው ያነጋግሩን